በወንድም ማስረሻ

ኤፌሶን 2 : 10
" እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።"

መጀመሪያ ከነበርንበት ማንነት ከሙታንነት ወደ ህይወት የመጣነው እግዚአብሔር የቀደውን ስራ እንድንሰራ እንጂ ዝም ብለን እንድንኖር አይደለም።
2 ጢሞቴዎስ 4 (2 Timothy)
7፤ መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤
8፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።
ጳውሎስ የዳነበትን ዓላማ ፈፀሞ አለፈ።
የተጠራንበት ዓላማ እኛ ከምንጨነቅለት ምድራዊ ኑሮ እጅግ ያለፈ ነው።
የብዙዎቻችን ህይወት ያለው ሮሜ 7 ላይ ነው፣ እንዲህ ይላል።
ሮሜ 7 (Romans)
14፤ ሕግ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለንና፤ እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ።
15፤ የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም።
16፤ የማልወደውን ግን የማደርግ ከሆንሁ ሕግ መልካም እንደ ሆነ እመሰክራለሁ።
17፤ እንደዚህ ከሆነ ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው እንጂ።
18፤ በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም።
#ሀጢያት በውስጣችን ከማደሩ የተነሳ የምናደርገው የምንወደውን የፅድቅ ስራ ሰይሆን የሀጢያትን ስራ ነው።
ለምን???
ጽድቅን ማድረግ እንወዳለን ፣ ግን አንችልም ምክንያቱም አዕምሮአችን ገና አልተለወጠም።
ሮሜ 12 (Romans)
1፤ እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።
2፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።
ሐዋርያው ለምን ይለምነናል?
# የተደረገልን ነገር እጅግ ብዙ ስለሆነ ያንን ስናስተውል ምን ማድረግ እንዳለብን እናስተውላለን።
ይህ እውነት ቢገባን አኗኗራችን በታደሰ ማንነት ይሆናል።
በዕምሮ መታደስ መለወጥ ምን ማለት ነው?
ከሀይማኖት መልክ ማንነት መውጣት ።
የተጠራንለትን ህይወት መኖር፣ ስርዓት ከመፈፀም ይልቅ በውስጥም በውጪውም ማንነታችን ክርስትናን መኖር።
#ሰውነትን ቅዱስ መስዋዕት አድርጎ ማቅረብ!
ከዚህ የተሻለ ህይወት የለም ፣ የገባው ሰው ለገባው ዕውነት ማንነቱን ይሰጣል።
ከዓለማዊነት አስተሳሰብ እንላቀቅ።
ማቴዎስ 17 (Matthew)
1፤ ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው።
2፤ በፊታቸውም ተለወጠ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፥ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ።
#ጌታ በፊታቸው ተለወጠ፣ ወደማንነቱ ተለወጠ
እኛ ደግሞ
2 ቆሮንቶስ 3 (2 Corinthians)
18፤ እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።
መለወጣችን ሂደት ነው ......ከክብር ወደ ክብር ወይም ወደ ክርስቶስ መልክ እየተለወጥን እየተለወጥን እንሄዳለን።

ዛሬ ማንን እየመሰልን ነው? መለወጣችን የቱ ጋር ደርሷል? እየተለወጥን ነው? ወይስ ገና ነን? ማንን እየመስል ነው?
በመለወጥ ሂደት ላይ ካልሆንን ዛሬ ወደመለወጥ እንመለስ ከሀይማኖተኝነት እንውጣ።
መንፈሳዊ ነገራችን ማደግ አለበት፣ እየተለወጠ መሄድ አለበት።

ደቀ - መዝሙር መሆን ለምን አስፈለገ?

ማቴዎስ 13 (Matthew)

10፤ ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፡— ስለ ምን በምሳሌ ትነግራቸዋለህ? አሉት።

11፤ እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፡— ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፥ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም።

ልጁን የሚመስሉ ቅዱሳን እንዲበዙ ፣ ከእኛ የሚቀጥሉት ልጁን እንዲመስሉ እግዚአብሔር ስለሚፈልግ ደቀ- መዝሙር እንድንሆን ፈልጓል።

ዛሬም አልረፈደም ፣ እግዚአብሔር እውነተኛ ደቀ -መዝሙር እንድንሆንለት ይፈልጋል።
አሜን ጌታ ይርዳን!!!